www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 27
ADDIS ABABA 5th, February 2019

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፪ /፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ....ገፅ ፲ሺ፱፻፹፪

CONTENT

Proclamation No.1102 /2018

Reconciliation Commission Establishment Proclamation.....page 10982

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፪/፪ሺ፲፩

የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ምክንያት በህዝቦች መካከል የተደራረቡ የቁርሾ ስሜቶችን ለማከም እውነትና ፍትህ ላይ መሰረት ያደረገ እርቅ ማውረድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶች የተረጋገጡትን መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ እና ተግባራዊ ለማድረግ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ጉልህ የመብት ጥሰቶችን ምንነት በግልጽ መለየት አስፈላጊ ስለሆነ እና ለእርቀ ሰላሙም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ፤

በተለያዩ ጊዜዎች እና የታሪክ አጋጣሚዎች የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ሌላ በደል ተጠቂዎች የሆኑ ወይም ተጠቂዎች ነን ብለው የሚያምኑ ዜጎች በደላቸውን የሚናገሩበትና በደል ያደረሱ ዜጎች ላደረሱት በደል በግልፅ በማዉጣት የሚፀፀቱበት እና ይቅርታ

PROCLAMATION No. 1102 /2018

A PROCLAMATION TO ESTABLISH RECONCILATION COMMISSION

WHEREAS, it is necessary to reconcile based on truth and justice the disagreement that developed among peoples of Ethiopia for years because of different societal and political conflict;

WHEREAS, it is necessary to identify and ascertain the nature, Cause and dimension of the repeated gross violation of human rights so as to fully respect and Implement basic human rights recognized under the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and international and continental agreements which Ethiopian ratified and since it is important for the reconciliation;

WHEREAS, it is believed that providing victims of gross human rights abuses in different time and historical event with a forum to be heard and perpetrators to disclose and confess their actions as a way of reconciliation and to achieve lasting peace;

www.chilot.me

የሚጠይቁበት መንገድ በማበጀት እና እርቀ ሰላም በማዉረድ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ፤

ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣ እየፈረሰ የሚሰራ ሳይሆን እየተገነባ የሚሄድ ስርዓት ለመፍጠር፣ ዲሞክራሲያዊ ሀገርና ማህበረሰብ ለመገንባት ሰፊና ተቀባይነት ያለው የእውነትና የእርቅ እና የሰላም ዓላማ ያነገበ፣ለግጭትና ቁርሾ ምክንያት የሆኑትን ዝንፈቶች ምክንያቶችና የስፋት መጠን አጣርቶ እውነታውን በማዉጣት ተመልሰው እንዳይመጡ በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን የሚወስድና እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመነጭ ገለልተኛ እና ነጻ ኮሚሽን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፪/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ ክልል ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) መሰረት በክልልነት የታወቁት ሲሆኑ አዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

፪/ "መንግስት" ማለት እንደአግባቡ የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ነው፡፡

፫/ "እርቀ ሰላም " ማለት በተለየ ምክንያት በተፈጠረ ግጭት፣ያለመግባባት፣ቁርሾ እና ጥላቻ አዘል ብቀላ በመያዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ የግጭት፣የጥላቻ መነሻ የሆኑትን በመለየት ላለፈው ይቅርታ፣ለቀጣይ ደግሞ ዘላቂ ፍቅር፣አብሮ የመኖርን እና የመቻቻልን እሴት የሚሰፍንበትን ሁኔታ መፍጠር ማለት ነው፡፡

WHEREAS, it is necessary to establish free and independent institution that inquire and disclose the truth of the sources, causes and extent of conflicts and that takes appropriate measures and initiate recommendation that enable for the lasting peace and to prevent the future occurrence of such conflict.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Reconciliation commission establishment Proclamation No.1102 /2018."

2. Definition

Unless the Context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "Region" means any of those recognized as a Region under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and include the Addis Ababa City Administration and the Dire Dawa city Administration.

2/ "Government" mean the Federal or a Regional Government.

3/ "Reconciliation" means establishing values of forgiveness for the past, lasting love, solidarity and mutual understanding by identifying reasons of conflict, animosity that are occurred due to conflicts, misapprehension, developed disagreement and revenge.

www.chilot.me

፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. መቋቋም

፩/ የዕርቀ-ሰላም ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ኮሚሽኑ የራሱ ጽሕፈት ቤት፣ በጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፫/ የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ሕጋዊ ሰዉነት አለው፡፡

፬/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፬. የኮሚሽኑ አባላትና አሰያየም

፩/ የኮሚሽኑ አባላት ቁጥር በመንግስት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ሌሎች አባላት በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ይሰየማሉ::

፫/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የኮሚሽኑ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል::

፭. የኮሚሽኑ ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ሰላም፣ ፍትህ፣ ብሄራዊ አንድነትና መግባባት፣ እንዲሁም እርቅ እንዲሰፍን መስራት ነው፡፡

፮. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ስራዉን በሚመለከት ማንኛዉም ያገባኛል የሚል ሰው ወይም አካል ሃሳቡን እንዲያቀርብ ጥሪ ማቅረብ እና አስፈላጊውን ምዝገባ ማካሄድ፤

፪/ ስራዉን በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ተደራሽ፣ አሳታፊ፣ ሁሉም አካል እኩል ተደማጭ የሚሆንበት የዕርቀ-ሰላም ውይይት መድረክ ማዘጋጀት፤

4/ Person" shall mean any physical or juridical person.

3. Establishment

1/ The Reconciliation Commission (hereinafter referred to as" The Commission") is hereby established by this Proclamation.

2/ The Commission shall have its own office, budget and necessary staff.

3/ Office of the Commission shall have legal personality.

4/ The Commission shall be accountable to the Prime Minister.

4. Appointment of members of the Commission

1/ Number of members of the commission shall be determined by the government

2/ Chairperson, Deputy Chairperson and other Members of the Commission shall, up on recommendation by the Prime Minister appointed by the House Of People's Representative

3/ The Head Of The Office serve as the Commission's Secretariat.

5. Objectives of the Commission

Objective of the Commission is to maintain peace justice, national unity and consensus and also Reconciliation among Ethiopian Peoples.

6. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following Powers and Duties:

1/ Concerning its work announce and make every concerned person or body to present his idea and the necessary registration.

2/ Make its work accessible, participatory by using technology; organize Reconciliation work shop in which all parties to be hear of;

www.chilot.me

፫/ የተለያየ አቋም የያዙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየትና ለሃገራዊ እርቅ መሰረት የሚሆኑ የጋራ መርህዎችንና እሴቶችን መለየት፤

፬/ የግጭቶችንና የመብት ጥሰቶቹን መነሻ ምክንያት ለመለየት ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶችን፣ የተጎጂዎችንና ጥፋተኞቸን አስተያየት በመወሰድ ማጣራት ማካሄድ፤

፭/ ለሰራው አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛዉንም የሰነድ ወይም ሌላ መረጃ ለአገር ደህንነት ሲባል በሚስጥር እንዲጠበቁ በህግ ጥበቃ ከተደረገላቸው ውጪ ከመንግስትም ይሁን ከማናቸውም ሌላ አካላት የመቀበልና በፈለገው ጊዜ እንዲያቀርቡ የማዘዝ፤

፮/ ሀላፊነቱን ለመወጣት የማናቸውንም ተቋም ይዞታ የመጎብኘት፣ በጉብኝቱም ጊዜ የሚያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃዎችና፣ ሰነዶችን ቅጂ የመውስድ፤

፯/ መረጃ ለመሰብሰብ በተናጠልም ሆነ በቡድን፣ በምስጢርም ሆነ ለህዝብ ክፍት በሆነ ሁኔታ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ መጥሪያ በመላክ ማንኛዉም ሰው እንዲቅርብ የማዘዝ እና ቃሉን በቃለ መሃላ እንዲሰጥ የማድረግ፤

፰/ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንድሁኔታው የፌደራልም ሆነ የክልል ፖሊስ እገዛ የማግኘት፤

፱/ በማጣራት የሚደርስባቸውን መደምደሚያዎች እንደሁኔታው በየጊዜው ለህዝብና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማሳወቅ፤እና

፲/ በህዝቦች መካከል የተፈጠረ ልዩነት እንዲረግብ እና መግባባት እንዲፈጠር እርቀ ሰላም እንዲወርድ የማድረግ።

3/ Identify principles and values which will be base for national Reconciliation by making discussion with groups of society which have different view;

4/ Make examination to identify the basic reasons of disputes and violations of human rights by taking into consideration of political, social and economic circumstances and the view of victims and offenders;

5/ To take or order presence of any document or information from government or anybody which the commission deemed necessary for its work except those that are given legal protection as confidential for the sake of national security ;

6/ To visit premise of any institutions and to take copy of any information and document found by its visit;

7/ To collect information make interview either individually or in a group in secret or in an open way to the public; order the presence of anyone through summon and require to give his statement through oath;

8/ Depending on the situations to get support from federal or regional state police to execute its duties;

9/ Notify to the public and concerned government organs the conclusions reached through the examination as appropriate; and

10/ Make Reconciliation among peoples to narrow the difference created and to create consensus.

www.chilot.me

፯. የኮሚሽኑ ስብሰባ

፩/ የኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ በየአስራ አምስት ቀኑ ይካሄዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ ከኮሚሽኑ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የኮሚሽኑ ምክረ ሃሳቦች በስምምነት ያልፋሉ፡፡

፬/ በምክረ ሀሳቦቹ ላይ የጋራ ስምምነት የማይደረስ ከሆነ በአብላጫ ድምፅ ያልፋሉ፡፡

፭. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚሽኑ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፰. የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፡-

፩/ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴዉን በበላይነት ይመራል፡፡

፪/ ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆኑ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የመድባል፡፡

፫/ ኮሚሽኑን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

፱. የኮሚሽኑ ምክትል ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የኮሚሽኑ ምክትል ሰብሳቢ፡-

፩/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢዉን ተክቶ ይሰራል፤

፪/ ሰብሳቢው የሚሰጡት ተግባራት የፈጽማል::

፲. የጽህፈት ቤቱ አቋም

የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት:-

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ሃላፊና ፤እና

፪/ አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. Meetings of the Commission

1/ The Commission shall hold its regular meetings every fifteen days; provided, however that it may hold extraordinary meetings at any time where necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the commission are present at a meeting.

3/ The Council shall pass its recommendation by consensus.

4/ In case of failure to reach consensus on recommendations, decisions shall be made by majority vote.

5/ without prejudice to the provisions of this Article, the Commission may adopt its own rules of procedure.

8. Powers and duties of the chair person of the commission

Chairperson of the commission shall:

1/ Direct the general activities of the commission;

2/ Assign the necessary supportive staff to the commission; and

3/ Make relation with third parties representing the Commission.

9. Powers And Duties of the Deputy Chair Person Of The Commission

The Deputy Chairperson Of The Commission shall:

1/ Perform the activity of the chairperson in his absence.

2/ Perform other activity given to him by the Chairperson.

10. Organization Of The Office

Office of the Commission shall have:

1/ Head appointed by the Chairperson Of The Commission; and

2/ The necessary staff.

www.chilot.me

፫/ የኮሚሽኑ ዋና ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል::

፲፩. የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ለኮሚሽኑ አጠቃላይ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣል፤

፪/ ለኮሚሽኑ የህዝብ ተሳትፎና ምክክር መድረኮችን የሎጅስቲክስ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫/ የኮሚሽኑን ቃለ ጉባኤዎች፣ ውሳኔዎችንና ሌሎች ሰነዶችን በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፬/ የኮሚሽኑን ስራ ለማሳለጥ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል።

፲፪. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

የጽ/ቤቱ ኃላፊ :-

፩/ የጽሕፈት ቤቱ ሥራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል፤

፪/ የኮሚሽኑ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል::

፲፫. የኮሚሽኑ ገለልተኝነት

ኮሚሽኑ ስራውን በነፃነትና በገለልተኝነት ያከናውናል።

፲፬. የስራ ዘመን

፩/ የኮሚሽኑ የስራ ዘመን አስከ ፫ ዓመት ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተጠቀሰው ቢኖርም የኮሚሽኑን የስራ ዘመን እንድሁኔታው ሊራዘም ይችላል።

3/ The head office of Commission shall be in Addis Ababa and may have branch offices at regions, as may be necessary.

11. Powers And Duties Of Office

The Office shall have the following Powers and Duties:

1/ Render general financial and administrative service to the Commission;

2/ Provide logistics support to the Commission on public participation and discussion forum;

3/ Register and keep minutes, decisions and other documents;

4/ To give necessary support and assistance to facilitate activities of the commission.

12. Powers And Duties Of The Office

The Head of the Office shall:

1/ Direct and administer the activities of the Office;

2/ Prepare the work programs and budgets of the Commission and implement same upon approval;

3/ Represent the Office in all dealings with third parties.

13. Independency Of The Commission

The Commission shall perform its activities freely and independently.

14. Terms Of The Commission

1/ Terms of the Commission shall be up to three years.

2/ Without prejudice to Sub-Article 1 of this article, term of the Commission may be prolonged as may be necessary.

www.chilot.me

፲፭. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚያቀርበው ማንኛውንም ህጋዊ ጥያቄ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

፲፮. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

፲፯. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፲፰. ጠቋሚዎችንና ምስክሮችን ስለመጠበቅ

፩/ ማንኛዉም ሰው በኮሚሽኑ ፊት ቀርቦ በሚሰጠው ቃል መሰረት ክስ ሊመሰረትበት እንደዚሁም የሰጠው ቃል በእርሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

፪/ ለጠቋሚዎችና ለምስክርች ጥበቃ ለማድረግ የወጣ ሕግ ለኮሚሽኑ ቃላቸው እና መረጃ ለሚሰጡ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል::

፲፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚንስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

15. Duty to Cooperate

Any person shall have an obligation to cooperate with the Commission for any legal questions requested by the Commission to enable to Commission undertake its responsibility provided under this Proclamation.

16. Budget

The budget of the Commission shall be allocated by Government.

17. Books of Accounts

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Commission shall be Audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

18. Protection Of Witnesses And whistle-blower

1/ No one may be accused by the testimony given to the Commission as well as the testimony given before the Commission could not serve as and evidence up on him.

2/ The provisions of the laws for the protection of the witnesses and whistle blowers shall apply to those who have provided testimonies and evidences to the Commission.

19. Power To Issue Regulation and Directive

1/ Council of Ministers may issue Regulations necessary for the effective implementation of this Proclamation.

2/ The Commission may issue Directives necessary for the effective implementation of This Proclamation and Regulations issued under Sub Article 1 of this Article.

www.chilot.me

፳. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

20. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come in to force as of the 25th day of December 2018 of its ratification by the House Of Peoples Representatives.

Done at Addis Ababa, 5th, Day Of February 2019,

SAHLEWORK ZEWEDIE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

www.chilot.me

1